የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 16
ADDIS ABABA 17th February2014

ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር ፰፻፳፪/፪ሺ፮ ዓ.ም**

**የዓለም የጤና ድርጅት የትምባሆ ቁጥጥር ማዕቀፍ ኮንቬንሽን ማፅደቂያ አዋጅ ....................ገጽ ፯ሺ፪፻፵፯**

**CONTENTS**

**Proclamation No. 822/2014**

**World Health Organization Framework Convention on Tobacco Control Ratification Proclamation ... Page 7247**

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፳፪/፪ሺ፮

## የዓለም ጤና ድርጅት የትምባሆ ቁጥጥር ማዕቀፍ ኮንቬንሽንን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የዓለም ጤና ድርጅት እ.አ.አ ሜይ ፳፩ ቀን ፪ሺ፫ በጄኔቫ የትምባሆ የቁጥጥር ማዕቀፍ ኮንቬንሽንን ያወጣ በመሆኑ፤

ይህንኑ ኮንቬንሽን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፲፫ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የዓለም የጤና ድርጅት የትምባሆ ቁጥጥር ማዕቀፍ ኮንቬንሽን ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፳፪/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. የኮንቬንሽኑ መፅደቅ

እ.አ.አ ሜይ ፳፩ ቀን ፪ሺ፫ የዓለም የጤና ድርጅት ያወጣው የትምባሆ የቁጥጥር ማዕቀፍ ኮንቬንሽን በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## PROCLAMATION No. 822/2014.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE WORLD HEALTH ORGANIZATION FRAMEWORK CONVENTION ON TOBACCO CONTROL

WHEREAS, the World Health Organization Framework Convention on Tobacco Control has been adopted at Geneva on the 21st day of May,2003;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Convention at its session held on the 21st day of January, 2014;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "World Health Organization Framework Convention on Tobacco Control Ratification Proclamation No. 822/2014".

### 2. Ratification of Convention

The World Health Organization Framework Convention on Tobacco Control adopted at Geneva on the 21st day of May, 2003 is hereby ratified.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazette P.O.box 80,001

## ፫. <u>የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ሥልጣን</u>

የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ኮንቬንሽኑ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 3. <u>Power of the Ethiopian Food, Medicine and Health Care Administration and Control Authority</u>

The Ethiopian Food, Medicine and Health Care Administration and Control Authority is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Convention.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of February, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት